የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ መጋቢት ፬ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

26th Year No. 24
ADDIS ABABA, 13rd, March, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፯/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ለመጠበቅና ድጋፍ የማድረግ የአፍሪካ ህብረት ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት) ማጽደቂያ አዋጅ…………………ገጽ ፲፪ሺ፪፻፸፬

## CONTENT

PROCLAMATION No. 1187/2020

African Union Convention for the Protection and Assistance of Internally Displaced Persons in Africa Ratification Proclamation ………………………………..…Page 12274

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፯/፪ሺ፲፪**

**በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ጥበቃና ድጋፍ የማድረግ የአፍሪካ ህብረት ስምምነት (የካምፓላስምምነት) ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን የመጠበቅና ድጋፍ የማድረግ የአፍሪካ ህብረት ስምምነት (የካምፓላስምምነት) ጥቅምት ፲፪ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም በካምፓላ ኡጋንዳ ስምምነት የተደረሰበት በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ስምምነቱን ጥቅምት ፲፪ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም የፈረመው በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮቸ ምክር ቤት የካቲት ፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው አስቸኳይ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታወጇል።

**PROCLAMATION NO 1187/2020**

**PROCLAMATION TO RATIFY THE AFRICAN UNION CONVENTION FOR THE PROTECTION AND ASSISTANCE OF INTERNALLY DISPLACED PERSONS IN AFRICA (KAMPALA CONVENTION)**

**WHEREAS,** the African Union Convention for the Protection and Assistance of Internally Displaced Persons in Africa was adopted in Kampala, Uganda on 22 October 2009;

**WHEREAS,** the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia signed the Convention on 22 October 2009;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 13th day of February , 2020;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ ”በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን ለመጠበቅናድጋፍ የማድረግ የአፍሪካ ህብረት ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት) ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፯/፪ሺ፲፪” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጥቅምት ፲፪ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም የተፈረመው በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎችን የመጠበቅና ድጋፍየማድረግ የአፍሪካ ህብረት ስምምነት (የካምፓላ ስምምነት) በዚህ አዋጅ ጸድቋል::

**፫. <u>በስምምነቱላይ የገቡ ተዓቅቦዎችእና መግለጫዎች</u>**

፩/የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሚከተሉት የስምምነቱ አንቀጾች ላይ ተአቅቦ አድርጓል፤

ሀ)የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የስምምነቱን አንቀጽ ፲፪ (፪) ላይ ተዓቅቦ አስገብቷል፡፡ ካሳ የሚከፈለው ለህዝብ ጥቅም ተብሎ የግል ቦታ በመወሰዱ በሚደርስ መፈናቀል ወቅት ነው፡፡ በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ መንስዔዎች ለሚደርስ መፈናቀል መንግስት የሚኖርበት ግዴታ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ ፹፱ (፫) በተደነገገው መሰረት ድጋፍ ማድረግ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

ለ)በግለሰቦች ወይም በተቋማት ሕግ የጣሰ ድርጊት መንስኤነት ተፈናቃዮች ድጋፍ ሳይደርሳቸው ቢቀር መንግስት በአንቀጽ ፲፪(፫) ያለበትን ግዴታ የሚረዳው ጥፋተኞች ተጠያቂ እንዲሆኑ የማድረግ እና የድጋፍ አቅርቦትን የማስቀጠል እንደሆነ ነው፡፡

ሐ)የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በስምምነቱ አንቀጽ ፳፪ በተደነገገው የአፍሪካ የሰዎች እና ህዝቦች መብቶች ፍርድ ቤት ስልጣን

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “African Union Convention(Kampala Convention) for the Protection and Assistance of Internally Displaced Persons in Africa Ratification Proclamation No. 1187/2020.”

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The African Union Convention for the Protection and Assistance of Internally Displaced Persons in Africa signed by the Federal Democratic Republic of Ethiopia on 22 October 2009 is hereby ratified.

**3.<u>Reservations and Declarations entered into the Agreement</u>**

1/The Federal Democratic Republic of Ethiopia entered reservations onthe following provisions of the Convention.

a) The Federal Democratic Republic of Ethiopia enters its reservation on Article 12 (2) of the Convention. Compensation is due when displacement results from expropriation procedures. The duty of the state in the case of displacement due to natural and man-made causes is seen within the purview of providing assistance as provided under article 89 of the Constitution and ensuring rehabilitation.

b) In the event of non- delivery of assistance to displaced populations due to the act or omission of individuals or entities that act in contravention with the law, the Government of Ethiopia understands its obligation under Article 12(3) of the Convention to be the obligation to ensure accountability of the perpetrators and resumption of assistance to the victims.

c) The Federal Democratic Republic of Ethiopia does not consider itself to be bound by Article 22 of the Convention on the jurisdiction of the African

 ነይሆንም፡፡

፪/የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሚከተሉት የፕሮቶኮሉ አንቀጾች ላይ መግለጫ አስገብቷል፤-

ሀ)የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአገር ውስጥ መፈናቀልን የሚረዳው በስምምነቱ አንቀጽ ፩(ተ) በተቀመጠው ትርጓሜ መሰረት ነው፡፡

ለ)የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ የአፍሪካ ህብረት እና ሌሎች ሰብአዊ ድርጅቶች ለተፈናቃዮች ጥበቃ እና ድጋፍ መስጠት የሚችሉት መንግስት የቅድሚያ ፈቃድ ከሰጠነው የሚለውን መግለጫ ያስገባል፡፡

ሐ)የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የስምምነቱን አንቀጽ ፭(፮) የሚረዳው ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው የጄኔቫ የሰብአዊነት ሕግ ሰምምነቶች እና ተጨማሪ ፕሮቶኮሎቻቸው መሰረትነው፡፡ የአለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ የማቅረብ ሚና ተግባራዊ የሚሆነው መንግስት በሚያቀርበው ጥያቄ እና በሚያስቀምጠው አሰራር መሰረት ነው፡፡

መ)የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፈጣን እና ያልተደናቀፈ የእርዳታ ጭነቶች፣ መሳሪያዎች እና ባለሙያዎች ዝውውርን የሚመለከተውን የስምምነቱን አንቀጽ ፭(፯) ተግባራዊነት የሚረዳው መንግስት በሚያስቀምጣቸው የጤና፣ የደህንነት እና የጸጥታ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ እንደሚተገበር ነው፡፡

## ፬.አስፈጻሚ አካል

የኢትዮጵያ ፌደደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰላም ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ፕሮቶኮሉን የማስፈጸም እና የመከታተል ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

Court of Justice and Human Rights.

2/The Federal Democratic Republic of Ethiopia entered declarations on the following provisions of the Convention.

a)The Federal Democratic Republic of Ethiopia understands the definition of internal displacement within the definition provided under article 1 (k).

b)The Federal Democratic Republic of Ethiopia declares the United Nations, the African Union and other humanitarian organizations may provide protection and assistance to internally displaced persons with prior permission or approval of the government.

c)The Federal Democratic Republic of Ethiopia understands Article 5(6) of the Convention in light of the Geneva Conventions and the Additional Protocols ratified by Ethiopia. It also construes the roles of international organizations to provide assistance based on the request and the arrangements put in place in consultation with the Government.

d) The Federal Democratic Republic of Ethiopia declares Article 5(7) of the Convention on the rapid and unimpeded passage of all relief consignments, equipment, and personnel to internally displaced persons will be applied in line with the health, safety, and security preconditions the government puts in place.

## 4. Implementing Organ

The Ministry of Peace of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is given the responsibility to cooperate with other relevant organs to implement and follow-up the Convention.

**፭.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበትቀን ጀምሮ የፀናይ ሆናል::

**አዲስ አበባ መጋቢት ፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**<u>5.Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 13th day of March , 2020.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**